# በTakoma Park Middle School የEast Silver Spring፣ Piney Branch፣ Sligo Creek፣ እና Takoma Park የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ስለ ክልል አጠቃላይ ሪፖርት ለሕዝብ መረጃ የሚሰጡ ስብሰባዎች

***7611 Piney Branch Road, Silver Spring, Maryland***

- **የመጀመሪያ የመረጃ ልውውጥ ስብሰባ - እ.ኤ.አ. በ የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም.**
- **የኮሚቴ የግምገማ/ክለሳ አማራጮች - እ.ኤ.አ. ግንቦት 27 ቀን 2009 ዓ.ም.**

**ሁለቱም ስብሰባዎች - ከ7፡30 pm እስከ 9፡00 pm ይካሄዳል።**

---

የቀድሞ መነሻ

እ.ኤ.አ. ከ መጋቢት 27 2006 ዓ.ም. ከማህበረሰቡ የተገኙትን ገንቢ አስተያየቶች ተከትሎ የBoard of Education (የትምህርት ቦርድ) የ East Silver Spring Elementary School የቅድመ ኬ 5 (በወቅቱ የቅድመ ኬ-2 የነበረው) ደረጃ እውቅና ከመስጠቱም በላይ እንዲሁም ተጨማሪ ህፃናትን ለመቀበል ተጨማሪ ስምንት ክፍሎች እንዲሰሩ ወስኗል። የBoard of Education በተጨማሪ የSligo Creek Elementary School እና Takoma Park Elementary School ከአቅም በላይ አጠቃቀምን ግምት ውስጥ በማስገባት በTakoma Park Elementary School አስራስድስት ተጨማሪ ክፍሎች እንዲገነቡ/እንዲሰሩ ወስኗል። ይህ የተጨማሪ ክፍሎቹ ግንባታ በወደፊት የክልል ጥናት ውስጥ በSligo Creek Elementary School የነበረውን ከአቅም በላይ አጠቃቀም ችግር ጨምሮ ከበቂ በላይ እንዲቀርፍ የታቀደ ነው።

የክልል ጥናት

እ.ኤ.አ. በሕዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም. የትምህርት ቦርድ ለክልል ጥናት የEast Silver Spring፣ Piney Branch፣ Sligo Creek፣ እና Takoma Park የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን እና ከእነሱ ጋር በተጓዳኝ ያሉ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣እንዲሁም በSilver Spring International እና Takoma Park በተጓዳኝ ያሉ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ክልል እንዲከልሱ ስልጣን ሰጥቶ ነበር። ሁለቱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በክለሳው የተጠቃለሉት፣ የSligo Creek Elementary School ከSilver Spring International Middle School የተያያዙ/የተገናኙ እስከ ሆነ ድረስ, እንዲሁም ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ከTakoma Park Middle School የተያያዙ/የተገናኙ ስለሆኑ ነው።

የክልል ክለሳ ሂደቱ የሚጀምረው የማህበረሰቡ አማካሪ ኮሚቴ፤ እ.ኤ.አ. ከመጋቢት እስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም. በሚያደርገው ስብሰባ ሲሆን፤ቀጥሎ እ.ኤ.አ. በጥቅምት አጋማሽ 2009 ዓ.ም. የሐላፊዎች ገንቢ አስተያየት ከቀረበ በሃላ፤ በመጨረሻም በBoard of Education እ.ኤ.አ. ሕዳር 2009 ዓ.ም. ክለሳ እና አፈፃጸም ይሆናል። ማንኛውም የክልል ለውጦች እ.ኤ.አ. ነሐሴ 2010፤ በEast Silver Spring እና Takoma Park የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ተጨማሪ ስራዎች እንደተጠናቀቀ፤ ተግባራዊ ይሆናል። ከDivision of Long-range Planning የሆኑ የMCPS አባላት የማህበረሰቡ አማካሪ ኮሚቴ እንቅስቃሴን/ሂደት ያመቻቻሉ። በዚህ በራሪ ወረቀት ለሕዝብ መረጃ የሚሰጡ ስብሰባዎች ማስተዋወቅ ስለ ሂደቱ በበለጠ ለማወቅ/ለመማር ዕድል የሚፈጥር ነው።

<u>በሁለቱም ስብሰባዎች ለእስፓኒሽ እና ለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የትርጉም አገልግሎት ይኖራል/ይሰጣል።</u>

ለየት ያሉ አገልግሎቶችን ለሚፈልጉ ግለሰቦች፤በተጨማሪም መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ ትርጉም ወይም ሌላ ልዩ ዕርዳታ ቢያስፈልግዎ፤ የFamily and Community Partnerships Unit በ ስልክ ቁጥር 301-279-3100 እና TDD (መስማት ለተሳናቸው) 301-279-3323 በመደወል ማነጋገር ይቻላል።

የክልል ክለሳ በሚካሄድበት ጊዜ፤ ከመነሻው እና የBoard of Education አፈፃጸም ሂደት ድረስ ያለው የፅሑፍ ማስረጃ በሚከተለው ድረ ገጽ የሚወጣ ይሆናል።

**www.montgomeryschoolsmd.org/departments/planning/CommunityInfo_Boundary.htm**